# ተቃዋሚዎችና ሚዲያዎቻቸው በኦሮሞ ወጣቶች ያላቸው አሳዛኙ ግንዛቤ!

## ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ)

በአለፈው ሰሞን "ሦስተኛው ዙር የኦሮሞ ፋሺዝም" ጹሑፌ በርካታ የምስጋና ደብዳቤዎች ደርሰውኛል። አመሰግናለሁ። በርከታዎቹ ደብዳቤዎቹ የሚናገሩት ስለ የኦሮሞ ፖለቲከኞችና የገዳ ስርዓት ምንነት የነበራቸው ግንዛቤ መቀየሩ ነግረውኛል። አዎን፤ ዛሬ ደግሞ የወያኔ ተቃዋሚዎችና ሚዲያዎቻቸው በኦሮሞ ወጣቶችም ሆነ በኦሮሞ ታሪክ ያላቸው የተጃጃለ (foolish) ግንዛቤ እንመለከታለን።

'ፓልቶክ' ክፍሎች ለመጎብኘት ሳት ብዬ ስገባ፤ የሚሰነዘሩ ግንዛቤዎች እጅግ የጫጩ ናቸው። እንደ ሰደድ እሳት በሁሉም "ክፍሎች" ማለት ይቻላል የሚሰነዘሩት ንግግሮች "ባሁኑ ሰዓት ዋናው ጠላቴ ወያኔ ነውና ወያኔ መጀመሪያ እናውርድ፤የሌሎቹ ፖለቲካ ወያኔ ሲወርድ የምንመለከተው ይሆናል" የሚል ነው። ይህ ግብዝ መስምር እንዲስፋፋ አስተዋጽኦ ያደረገው "ግንቦት 7" የተባለው ዱርዬና አታላይ ቡድን ነው። ግንቦት 7 ትምህርቱን የቀሰመው ለበርካታ አመታት ይህንን ማጃጃያ መስመር አጥብቆ ሲሰብከን ከነበረው ከ"ኦነጎች/OLF" ነው። ኦነግ ደግሞ ይህንን 'ስልት/ታክቲክ' የቀሰመው ከ"ወያኔዎች" ነው። ሦስቱም ይህንን ስልት ሲጠቀሙት የቻሉት፤ወያኔ ስልጣን ለመንጠቅ መጀመሪያ "ደርግን" እንጣል ሲል ነበር፤ ደርግ ጣለና ዋና ጠላት አድርጎ የፈረጃቸው "ድህነት፤ኦነግ፤ኦብነግ፤ግንቦት7፤ሻዕቢያ..." ናቸው። በሁለተኛ አስቀምጦአቸው የነበረው ክፍሎች ወደ አንደኛ ደረጃ ጠላት አድርጎ መድቦ እስካሁን ድረስ ስልጣኑ በሰላም መምራት አልቻለም። በሁለተኛ ደረጃ አስቀምጦአቸው የነበሩት ክፍሎች 'የህልውናው' ተፈታታኝ ሆነው አግኝቶአቸዋል።አስገራሚ የሚያደረገው ደግሞ' ወያኔ እነኚህ ክፍሎች (ኦነግ፤ ሻዕቢያና ኦብነግን) ፖለቲካቸውን በማስፋፋት ከፍተኛ ቅስቀሳ በማድረግና፤ አልፎም ፕሮግራማቸው እንዲተገበር ቡዱኖቹ ከጠበቁት በላይ ረድቶአቸዋል።ዞሮው ህልውናውን ተፈታተኑት!!

ግንቦት 7 የተባለው የተገንጣዮች አቀንቃኝ የሚመራው ኢሳት ደግሞ እንዲህ ዓይነቱ ማጃጃያ መስመር በስፋት የሚያስተጋባ ነው። ድርጅቱ ጸረ አገር መሆኑንና "አማራ ሆነው" ጸረ አማራ ግለሰቦች የሆኑ ያሉበት የተገንጣይ አደግዳጊ ሚዲያ መሆኑ ከጅምሩ የምናውቀው ነው። ተድላ አስፋው "ቪ ኦ ኤ" የተባለው የአሜሪካ ፖሊሲ አራማጅ "ማነፍሕ" የፕሮፓጋንዳ ጣቢያ፤ ጃዋር መሓመድ የተባለው "ኢትዮጵያዊአኖች ከኦሮሞ ክልል አንዲባረሩ" ጥሪ በማስተጋባት የታወቀው "የሁከት ሚሊሺያ መሪ" የሆነው አደገኛው ሰው፤ ቪ ኦ ኤ ጋብዞት

ስለነበር “አቶ ተድላ አስፋው” ይህንን አስመልክቶ “ለአሜሪካው መናፍሕ” ተቃውሞውን በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ ኢሳትን አስመልከቶ አንዲህ ብሎ ነበር፤

“Neamin Zeleke position is the G7 position. They talk with nothing back home. His movement is known for Talking a.k.a ESAT and I do not give any credibility for his group being a unifying factor. The ESAT broadcast is more a divider than a uniter. Their airtime is filled with *sensationalism incorporated with Kilil terminology*. The only thing we have is the name Ethiopia on their station.” አጽንኦት የተጨመረ።

እነዚህ የመሳሰሉ ሚዲያዎች የጠላት መሳሪያዎች እየሆኑ ነው። ሕዝቡም ግንዛቤ እንዳይኖረው ጫና አድርገዋል።የጣላት ዓይነት ቢኖሮውም፤መርህ የለቀቀ፤ከጠላት ጋር ትከሻ ለትከሻ እየተሻሹ፤ በየአዳራሹ እየዞሩ የጠላትን ፖለቲካ እየደገፉና የአማራ ሕብረተሰብ “ነፍጠኞች በቁጥጥራችን ስር አድርገንላችኋል” የሚሉ ጠላት ለማስደሰት፤ወገን ለማሳዘንና ግንዛቤ የጎደለው ክፍል እያሳሰቱ እንዲቀበላቸው ማድረጉ፤ በሁለተኛ ደረጃ የተመደቡ ጠላቶች የሚሏቸው (እንዲያውም አጋር እንጂ በጠላትነት ቀርቶ በጥርጣሬ እንኳ አያዩዋቸውም)። ይግረም ብሎ፤ ዋና ጠላት የተባለው ጠላት (“ወያኔ”) ሲወድቅ፤ ህልውናህን የሚፈታተኑት እነዚህ መሆናቸው ከታሪክም ከተሞኩሮ የታዬ ነው። ለዚህ ውድቀት ዓይነተኛ ሽንፈት የሆነው “መርህ አልባ” የትግል እንቅስቃሴና “አገራዊ ፍቅር” ያልታጠቁ መሪዎች ፖለቲካውን” ሲያራምዱ የሚከሰት አደጋ ነው። ጊዜያዊ ጥገና እና እርካታ የሚያመጣው ጠንቅ በጣም የከፋና ረዥም ቀውስን ያስከትላል።

አንድ ምሳሌ ልስጣችሁ። ‘መላው ህይወቱ ሰውን መግደል ያሳለፈው ‘የኮራፐት ክሪሚናል’ ኢሳያስ አፈወርቂን ተከለሰውነት ለመገንባት ሲዳክር የነበረው ‘አስቃባጩ’ የግንቦት 7 መሪው በአንዳርጋቸው ጽጌና አገር ወዳዱ የሙቶአለቃ አያልነው ደሴ መካካል በኢሳት ቲ/ቪ ስለ ተቃዋሚዎች አብሮ መስራት በሚመለከት የተደረገው ውይይት ተመልሳችሁ ብታደምጡ፤ “አንዳርጋቸው ጽጌ” ሉዓላዊ የአገር\ ሶቨርኒቲ/ አንድትን፤ዳር ድምርንና ሰንደቃላማን “እንደ ቅድመ ሁኔታ” መቀመጥ የለባቸውም የሚለውን ድረጅቱ በጽሑፍ የበተነውን መስምር፤ እውይይቱም ላይ ከመድገሙ አልፎ፤ “ግንቦት7” የሚከተለው “ፕሮግራምና መርህ” እንደሌለው “ለሥልጣንም” እንደማይታገል፡ የተከራከረበትን ስታደምጡ፤ ከላይ የተከሰቱ የወደፊት አደጋና ግርግር አፍላቂ ምክንያቶች የሚሆኑት ምንጮች እንደዚህ ያለ ‘መርሃ ቢስ’ ‘የጠላት አሰላለፍ ግንዛቤና’ ‘የአገር እንድነት መርህ’ የማያስቀምጥ ትግል፤ “ከጎኔ ጋር ቆሞ ወያኔን ለመጣል እየታገለ ያለው ጠላት” የሚባለው **“ምንም አይጎዳኝም/ ሥልጣን ሲገኝ በኋላ የምናየው ጉዳይ ነው”** በሚል ‘መርህአልባ’ ‘በይደር’ ያስቀመትከው ጠላት የባሰ

ግርርግርና መርዝ አሰራጪዎች የሚሆኑት እነሱ ናቸው። ለምሳሌ ወያኔ ይኼውላችሁ አንደ "ፍጥምጥማችሁ ተፈጣጠሙ" ብሎ ወደ ክልሉ ወደ ትግሬ ሪፑብሊክ ቢሄድ፤ አገር ገንጣዮቹ ሕዝብን በመፍጀት ሁሉንም ለመጥረግ ወደ ኋላ የማይሉ የመጀመሪያ ግርግር ፈጣሪዎች እነሱ አንደሚሆኑና "ምንም አያደርጉም" የተባሉ የሁቱና የቱሲ ዓይነት "ሞንስተሮች" አንደሚሆኑ እወቁ። ከኦሮሞ እና ኦጋዴን የሚባረሩት፤አገር ውስጥ ያሉ "ኢትዮጵያ" የሚሉ ተቃዋሚዎችና፤ "የእነ ግንቦት7 አስቃባጭ ምስኪን ጀሌዎች" አንጂ 'መሪዎቹ" ግን ወደ አገር አንደማይዘልቁ ሳይታለም የተፈታ ነው።ገና ካሁኑኑ "የሰሚራ ቡና እና ዕጣን ሽታ እንጂ የጦርነት ባሩድ" ሳያሸቱ "የመጀመሪያው ፊሽካ ነፋን" ባሉበት በሳልስቱ ወደ አሜሪካቸው መመለስ ጀምረዋል። ንዓሻ በሎ! ይላል ትግሬ "ሞኝህን ፈልግ!" ጥሩ አባባል ነው።

ማእከሉ ሲናጋ በተለይም የታጠቁ ክፍሎች ከሆኑ! የሚያመጡት ትርምስ ብዙ ነው። "ግድየለም" እየተባለ በቸልተኝነት በወዳጅነት እያየህ ቆይተህ፤ "ማእከሉ ሲናጋ"፤ የሚቆጣጠሩትም ሆነ ግርግር የሚፈጥሩት እነዚህ ክፍሎች ናቸው የምለው ለዚህ ነው። የእገሌ ድርጅት መሪ ከታጠቁ ተግንጣዮች ጋር አብሮ እየሰራ ነው! እያመጣቸው ነው፤ ወደ መሃል እየጎተታቸው ነው፤ ጎበዝ ድረጅት ነው የሚል የሰነፎች ሙገሳ እየተቸረው፤ ተገንጣይንና በተለይ በዘር ማጥፋት ወንጀል የተሳተፉትን 'በወዳጅነት መመልከቱ" ባሕሪያቸውን አለማወቁ ከፍተኛ ጠንቅ እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል።ወንጀለኞቹም፤ ከወንጀላቸው ለመሸሸግ የማያደርጉት ሙከራ የለም። ውንጀላቸው ያለፈ ወንጀል ነው። ያነን ማንሳት ሰላም አያመጣም፤ "ወከላጆቻችን ፤ዘመዶቻችን ገድለውብናል፤ እንፋረዳቸዋለን የሚሉ *ጠብ ጫሪዎች* *ለብጥብጥ የሚጋብዙ" ክፍሎች ብቻ ናቸው የሚቃወሙቸው" የሚሉ "ግብዞች አሉ"። አንዲህ ከሚሉ አንዱ "መረራ ጉዲና" ነበር። ባለፈው ሁለት አመት ውስጥ 'ይመሰልኛል' (ድምፁ ቀድቼዋለሁ) 'በአዲስ ደምፅ ራዲዮ' መረራ ጉዲና የተለመደው ቧልቱ "ሲቦተልክ" አድምጩዋለሁ (ዛሬ ኦሮሞዎች ሲገደሉ ግን ጮክ ብሎ ገዳዮች በሕግ ይጠየቁ ባዩ ቀዳሚው እሱ ነው) ።

አስገራሚው ግን ፖለቲከኞቹ የሚነግሩን "ወንጀለኛው እና ሽብር የሚፈጽመው "ወያኔ" ብቻ እንጂ ሌላ ሽብርተኛ የለም፡ እያሉ ወንጀለኛ ድርጅቶችን ሽፋን እየሰጡ ነው። ሕዝቡንም በዛው በተሳሳተው ጎዳና አንዲመላለስ እያደረጉት ነው። ይህ ሴራ በጥብቅ ማወቁ አስተዋይነትን ይጠይቃል። ወንጀላቸውን እየሸፈነክ "ወንጀል" ሰሪው "ወያኔ' ብቻ ነው ብሎ በሕዝብ ፊት በሚዲያ በቂ ሽፋን መለገስ "ተባባሪነት" ብቻ ሳይሆን መጻኢ ጊዜ "ተአማኒትን" ያሳጣል። ተጎጂዎችንም አጥቂዎቻቸውና ገዳያቸው አንዳያውቁ ማድረግ ነው።

እንዲህ ያለ አገራዊ መሰረት ለማናጋት የተሰለፉ የውስጥም የውጭም ጠላቶች በጥንቃቄ ካልተከታተልካቸው፤ በቸለተኝነትና "ወያኔ" ብቻ ይውደቅ እንጂ የሚል "ጊዜያዊ ጥገና" temporary fixation የሁለት ክፍሎች ጥምረት ማለትም "የሰነፎች ወይንም ተንኮለኛ" ፖለቲከኞች የሚከተሉት ስልት ነው። አጃቢዎቻቸውም በዛው ግንዛቤ በጎደለው አስተሳሰብ እየተከተሉ መርህ አልባ ሆነው፤ ዳግም ለሌላ ዙር "ግርግር" ይጋለጣሉ። አሁን እየተጓዝን ያለበት ሁኔታ ያንን ያመላክታል።

የዛሬው ኦሮሞ ወጣት ተማሪዎች እየተከተሉት ያለው እንቅስቃሴ "ባይተዋርነት" ያመነጨው የፖለቲካ ቀውስ ነው። ቀውሱ "ኪሳራ" ነው። ተቃዋሚዎቹም በዛው አክሳሪ እንቅስቃሴ በመጓዝ፤ "ወያኔ ይውደቅ እንጂ" በሚል ሂሳብ እየጓጉ 'አክሳሪ ፖለቲካ" እየተጓዙ ያሉትን 'ግንዘቤ የጎደላቸው ኦሮሞ ተማሪዎችና ከኋላ ሆነው እየገፏቸው ያለት "ፋሺስታዊ ተገንጣይ ክፍሎች" በሚዲያና በይፋ እያበረታቱ፤ የተገንጣዮቹ ፕሮፖጋንዳ በሚዲያዎቻቸው ሰፊ ሽፋን በመስጠት የኪሳራ ፖለቲካ እየተጓዙ እያየናቸው ነው።

ይህ የኪሳራ ጉዞ በቅርብ ለምናውቃቸው አዲስ ክስተት አይደለም። ተቃዋሚ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ የተገንጣይ ፋሺስት ፕሮፖጋንዳዎችና አገራዊ አንድነትን የሚጻረሩ አፍራሽ "የተገንጣይ ድርጅቶች መግለጫዎች" በየሚዲያው በስፋት ሲለጥፉላቸው ዓመታት አልፏል። ዛሬም ያንኑ እየደገሙት ነው። ኢትዮ-ሚዲያ በሚባለው "አፍቃሬ ኦሮሞ ተገንጣዮችና ፤ ጠባብ ትግራዋይነት" የሚያጠቃው ይህ ሚዲያ የነዚህን ክፍሎች ፕሮፖጋንዳ ሲለጥፍ፤ ሲያስተጋባ፤ሲክብ፤የፎቶግራፍና የቪዲዮ ስራዎች በስፋት እያሰራጨ ነው።

እሱ ብቻ ሳይሆን "ዘ-ሐበሻ" የተባለው ከተስፋዬ ገበረአብ ጀምሮ፤ በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ የተፈለፈሉ "አፍራሽ ተገንጣይ የሆኑ ፋሺስት ድርጅቶች" መግለጫዎችና የፕሮፖጋንዳ ስራዎች እንዲሁም ሰንደቃላማዎቻቸውና አርማዎቻቸው በሙሉ በሕዝብ ሕሊና እንዲቀረጹ ከፍተኛ የጠላት/የሳብቨርዥን ስራ ሲሰራ ብዙ አመታት አልፎታል።

በቅርቡም 'እንደ አቅሚቲ' "አረብ እንጂ ሶማሌ/አፍሪካ" አይደለንም በሚል (ካሁን በፊት ቃለ መጠይቁ በማስረጃ አቅርቤላችሁ ነበር፤ያንን አስታውሱ) መሪ የሚመራው ኦጋዴን ነፃ አውጪ የተባለው "ጸረ ኢትዮጵያ ደርጅት" ያደራጃቸው "ኦጋዴን ወጣት ተማሪዎች ሕብርት" OYSU: በእንግሊዝኛ የተጻፈ መግለጫ ስታነቡ " The Ogaden and Oromo people share a common struggle,….." የጋራ ትግላችን "መገንጠልን ነው" የሚለው ጸረ ኢትዮጵያ ፕሮፖጋንዳና እንዲሁም ድረገጹ በቪዲዮና በፎቶግራፍ ያጣበበው፤ የባይተዋሮቹ ኦሮሞ ተማሪዎች ቅንቅስቃሴ ፕሮፖጋንዳ ስራ ለዓለም እያስተጋባ ነው።

ይህ ክስተት ተቃዋሚውና ሚዲያው 'ኪሳራ' ውስጥ የሚዋኝ "መርህቢስ" ተቃዋሚና ሚዲያ መሆኑን ያመላክታል። ለኢትዮጵያን አንድነት "እቆማለሁ" እያልክ "የኢትዮጵያ አንድንትን" የሚጻረሩ "የተግንጣዮች መግለጫና የሚዲያ ሽፋን ከሰጠህ፤ ምኑ አገራዊ ተባልከው?" ሚዲያ

ወሳኝ መሆኑን የታወቀ ነው። ተገንጣዮቹ የሚዲያ ሽፋን ጠቃሚነቱን ስለሚያውቁና በዚህ ብልጦች ስለሆኑ እነዚያ ግብዝ የሚዲያ ተቋማትን እየተጠቀሙባቸው ነው። በተገንጣይ ሚዲያዎች ግን የነሱን ዓላማ እና ፕሪንስፐል፤ትግል የሚያጋልጥ፤የሚጻረር ብትልክላቸው "ከቶውንም፤ አያትሙትም"።

በቅርቡ ኢሳት የተባለው "አፍቃሬ ኢሳያስና ኦነግ የሰየማቸው የከተማዎች ስም ተቀብሎ የሚያስተጋባ የባንዳዎች ስብስብ" የሆነው 'ኢሳያስያዊ ሚዲያ-' "ጃዋርን የሚያክል" አደገኛ ሰውና ጸረ ኢትዮጵያ ወጣት፤ በቀርቡ ወደ ሚዲያው ጠርቶ ፕሮፓጋንዳውን ለኢትዮጵያ ኦሮሞ ወጣቶች ሲያስተላልፍለት እንደነበረ የምታውቁት ነው (መሳይ በተባለው እየተሞገሰ ማለት ነው)።ከዚህ ወዲያ ጸረ ኢትዮጵያነት ፍፁም ሊኖር አይችልም። ፕሮፓጋንዳ የጦርነት ግማሽ ሃይል ነውና "ግማሹን ጦርነት" ተቃዋሚዎች "ለኢትዮጵያ ተጻራሪዎች" እየሰሩላቸው ነው።

ተቃዋሚው "የፋሺስ ተገንጣዮችና በኢሳያስ አፈወርቂ የፕሮፓጋንዳ ካድሬዎች ድጋፍ" ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ማምጣት ይቻላል የሚለው እንቅስቃሴ የሚያጎላው ለምንድነው? የሚለው ጥያቄ ሰፊ ዝርዝር ውስጥ ያስገባናል። ባጭሩ ግን፤ዞሮ ዞሮ፤ የሚያመላክተው መርህ አልባ ከመሆናቸው (ዋናው ይህ ቢሆንም) ሌላ፤ አልፍ ብሎም "ትግሉን" የሚመሩት አገር ውስጥ ያሉ መሪዎች ጭራሽ ፈሪዎችና፤ ለመስዋእትነት ያልተዘጋጁ፤ 'ተምበርካኪዎች' ስለሆኑ፤ እነሱ የማይመሩት ማንኛውም "ቦግ" የሚል ወያኔን የሚጋፈጥ እንቅስቃሴ ሲከሰት "መርህ ይኑሮው አይኑሮው" ድጋፋቸውን ቶሎ ይሰጣሉ። ምክንያቱም እነሱ የሚጋፈጡበት ወላፈን ባለመሆኑ (ልክ ዲአስፖራ ያለው 'ግፋ በለው' መረህቢስ የሆነው "የግንቦትገ የፓልቶክ ተቃዋሚ ጀሌው" ዓይነት)_፤ ድጋፋቸውን መስጠት ብቻ ሳይሆን እንቅስቃሴው ***"ሰብአዊነትን፤የመብት ጥያቄንና አገራዊነትን ያላብሱታል"።*** ይህ በሽታ ተሎ ወደ ሚዲያዎች ይተላለፍና ከሚዲያዎች ወደ ፓልቶክ ዞሮ "የእንቅስቃሴው ምንነት ሳይመረመር" የመብት ጥያቄ ተብሎ ይደመደማል። ሆ ሆታው ዓለም ያዳርሳል። ከአስመራ "እንዳ ስሚራ ቡና ቤት፤ አመርቂ ቡና እየተፋላ" የተነፋው የፊሽካው መነፋት ሆ ሆታ የትከሳት "ግለት" እንደጦፎውና ባንዴ "አንደቀዘቀዘው" ዓይነት ክስተት! ያሁኑ ኦሮሞዎቹ የባይተዋርንት ቀንቅስቃሴም ተቃዋሚዎች ያላቸው እውቀት "አሳዛኝ ግንዛቤ" ነው የምለው ለዚህ ነው።

ታማኝ በየነ የተባለው የግንቦት 7 ሰው ሲለው የነበረው ይህንኑ ግንዛቤ ቢስነቱን ያንጸባርቃል። ምንም ይሁን ምንም የተማሪዎቹ እንቅስቃሴ የመገንጠል ነው ተብሎ እንደ አንዳንዶቹ የመገንጠል እንቅስቃሴ ፍላጎት ነው ቢሉም፤ "የመገንጠል ጥያቄ ባልደግፈውም፤ መብታቸው ነውና አከብርላቸዋለሁ"፤ ዲሞክራሲ ማለት የመብት ጥያቄ ነው ብሎናል። ዲሞክራሲና አገር ምን መሆኑንም ብዙ ዜጎች አልገባቸውም። ተማርን የሚሉ ክፍሎችም ዲሚክራሲ ከአገር ማፍረስና ያለማፍረስ ያያይዙታል። ዲሞክራሲ ባለፉት ቃለ መጠይቆቼ እንደገለጽኩት አገር ማፍረሻም፤ሂትለሮችና ፋሺስቶች ወደ ሥልጣን መወጣጫ የሚገለገሉበት ዘዴ ነው (የሂትለር ወደ ሥልጣን የመጣበትን መሳልል አስታውሱ)። ዲሞክራሲ፤ ከአገር አንድነትና ደህንነትጋር የሚገልጹ ተቃዋሚዎች የተበራከቱበት አገር ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ነው። ትምህርቱ ከየት አንዳገኙት አለውቅም። በተለይ "ሪፈረንደም" የሚል ሂደት

እንዲተገበር የሚጥሩ "ኢምፔሪያሊስቶች' መሆናቸው ታሪክ ይነግረናል። ለምን እንደሆነም የምናውቀው ነው። ሙልጭልጭ እያሉ አልገዛም እያሉ የሚያስቸግሩ 'ዲግኒፋይድ//ኩሩ' አገሮች፤ለማንበርከክ የአገሮች ቀላላል "የአይጥ መያዣ"/ ትራፕ / አይነት መሆኑ ነው። "ራስን በራስ ለመወሰን/ሪፈረንደም ይሉታል" ሱዳንም፤ፓኪስታንም፤ሶማሊም፤ ኤርትራም.......የተቀረቀቡበት ወጥመድ እንደማለት!

ዲሞክራሲ ሞንስተሮች የሚከተሉት በእራሱ ሂደት በየጊዜው እያበጃጀ እንደገና እራሱን የሚያቃጥልና የሚጻረር፤ ብዙሃን በአናሳ ወይንም በግለሰቦች መብት ላይ አመጽ የሚያስነሳ "ሞብ-ሩል" የሚያሰፍን ስርዓት የመሆኑንም ጭምር አይነግሩንም። አሜሪካን አይነት "የባንክ ባለሃብቶች" የሚቆጣጠሩት 'የኦሊጋርኪ' ስርዓት በዲሞክራሲ የሚጎናጸፉት ስልጣን እና ቁማር ተመልከቱት። ዲሞክራሲ አንኳን አገርን ለማቆየት፤ እራሱንም በተመሰረተበት ሕግ ለመቆየት ዋስትና የለውም። ማንም የታጠቀ ዱርዬ የሚጠለፈው፤ የሚፈርስ፤የሚተካ ነው። ለዚህም ክስተት ስንት ህይወት ተገብሮበታል።መጨረሻው ገዢው "ጥቂቶች" ወደ ምኞት አንደላቅቆ ሌላ አዙሪት ውስጥ የሚያስገባ በንትርክ የተከበበ ስርዓት።ግለሰቦች ሳይሆኑ ብዙሃን/ማጆሪቲ የሕግ ባለቤቶችና የበላይ የሚያደርግ። አናርኪ፤ሶስያሊስት፤ፋሺስት፤ ናዚዎች፤ ኮሚኒስት፤ካፒታሊሰት፤ዲሞክራትስ፤ሪፓብሊካን፤ ሞናርክ እና ልኡላን፤ሼኮችና ሙላሆች.......በበላይነት የሚመሩት የብዙሃን ደምፅ በጥቂቶች ህይወት ላይ የሚወስን! ዲሞክራሲ የነዚህ ሁሉ "ኦሊጋርክ" ክፍሎች የመጫወቻ ስልት ነው።

ዲሞክራሲ ሌላው አስፈሪው የሞንስተር ገጽታው "ብዙሃን በጥቂቶች ላይ የሚጭኑበት ዲክታተርሺፕ' እንደሆነም ልትገነዘቡት ይገባል። ኦሮሞዎችና ኦጋዴኖች እየጠየቁት ያለው ይህንኑ "የነገድ/ጎሳ ወይንም "ራስን በራስ ማስተዳደር መብት" ነው። በተለይ ደግሞ ዝቅ ሲል 'ነገድ ተሞርኩዞ' ራስን በራስ ለማስተዳደር የሚፈቅድ ዲሞክራሲ "አመጸኞች/ዱርዬዎች" እነሱን በማይመስሉ ነገዶችና ዜጎች ላይ የመብት መዳፈርን የሚያጎናጽፍ ሰርዓት ነው። ልገንጥል ያለ በጉልበት መያዝ አይቻልም፤ በዲሞክራሲ ረፈረንደም መብት ይሰጠውና ይለይለት፤ ወይንም "ራስን በራስ ሰዎች በሚመረጡ ሰዎች ብቻ የፌደራል መብታቸው ካስከበርክ ሰላም ይመጣል" የሚሉ ደካሞችና "እንዝህላልነት ያጠቃቸው ታላላቅ የውጭ አገር ሰዎችና ታላለቅ የአፍሪቃ ደራሲያን እና "ኖብል ተሸላሚዎች" ሲናገሩ አድምጩአለሁ።

መገንጠል ማለት አገርን ሰውን ቤተሰብን በሁለት በሦስት ከፋፍሎ፤ ታሪክን ሰላምን መግደል ማለት ነው። በራስ ሰው መተዳዳር ሌሎችን ነገዶችና ዜጎች ፍጹም አግላይ ከመሆኑ ሌላ፤ መገንጠል ከጀመረ፤ ያ ክልል የመገንጠል ፍላጎት እየተራባ፤እየተከፋፋለ "የት አንደሚቆም" ፤ ማቆሚያ ድምበርም የለውም። እስከ......ወዲያኛው እየተገነጣጠለ እራሱ በራሱ እያቃጠለ እያፈረሰ ሁከትን የሚያራባ "የዱር ሕሊና" የተሸከሙ ሰዎች "ፋንታሲ ዓለም" የሚሆነውም ለዚህ ነው። ፓኪሰታን/ምስራቅ/ምዕራብ ቤንጋሊ/ አፍጋኒስታን ከሕንድ ሲገነጠሉ ያጋጠማቸውና አሁንም ያላባራ መከራ የዚህ ውጤት ነው።ባጭሩ ግንጠላም ሆነ የነገድ ዲሞክራሲ፤ "ሽብር፤ግርግር" ማለት ነው። ሽብር መብት አይደለም። እነዚህ ክፍሎች በሽብር ወንጀል የምንከሳቸው የአማራን ሕዝብ ሰቆቃና ህይወት ያጠፉ ወንጀለኞች የሚመሩት እንቅስቃሴና የቀየሱት ትግል ነውና "ከመብት ጥያቄ ጋር አይገናኝም"።

ተቃዋሚዎችና ሚዲያዎች በሰሞኑ የኦሮሞ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ያላቸው አሳዛኙ ግንዛቤ ስል ምን ማለቴ ነው?

ኦሮሞ ተማሪዎች "ባይተዋሮች ናቸው፤ የሰሞኑ የኦሮሞ ተማሪዎች 'ባይተዋርነት' ያመጣው እንቅስቃሴ ነው። እንዲህ ስልስ ምን ማለቴ ነው? ሰሞኑ አንድ ምሁር ወዳጄ እሱን ከመሰለ ምሁር ወዳጁ በሰሞኑ ኦሮሞዎች እንቅስቃሴ ያደረጉትን የወዳጅነት ሃሳብ ልውውጥ ግንዛቤዬን እንዲጎለብት ብሎ የተነጋገሩበትን አንዳንዳንድ ውይቶችን አጫወተኝ። ሙሁሩ እንዲህ ይላሉ፦

"መቼም fantasy የኢትዮጵያ ልሂቃን መለዮ ነው።" (አሜሪካ ሜኔሶታ ውስጥ የሚኖር)ፕሮፌሰር እስቄል ገቢሳ ሰሞኑን በኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ ቀርቦ፤ "ይህ የኦሮሞ ተማሪዎች ንቅናቄ መሪ የለውም፣ ምክንያቱ እና መፍትሄው ምን ይመስሎታል?" ተብሎ ተጠየቀ። ህልመኛው የተደናገረው "ፕሮፌሰር" አንገቱን በኩራት አቅንቶ የምሁርነት ማመላከቻ መነጥሩን ሽቅብ ገፍቶ ተናገረ፤

"በታሪኩ ኦሮሞ የአንድ መሪ መህበረሰብ አይደለም፤ እ…ጥንትም ሆነ ዛሬ የኦሮሞ አብዮት የጋርዮሽ አብዮት ነው፡፡ መሪ አያስፈልገውም፡፡እንደውም የኦሮሞ ህብረተሰብ ነቅቶ መጠበቅ ያለበት አንድ መሪ እንዳይነሳ ነው፡፡ እ… የገዳ ስርዓት በኦሮሞ ህዝብ ደም ስላለ አንድ መሪ አያስፈልገውም… መሪው በደሙ ያለው የገዳ ስርዓት ነው፡፡" … ሲል ለተጠየቀው መለስ ሰጠ።

እስቄል እንደሚያልመውም ይህ አብዮትም ኦሮሚያን በመገንጠል በስኬት ሲጠናቀቅ ከሀያ አምስት አመታት በላይ የአሜሪካን ሊበራል ዲሞክራሲ ካጣጣመበት አመሪካ ከሌሎች ሌሎች ጓዶቹ ጋር በመሆን የአዲሲቷን ኦሮሚያ "የቦኩን" በትረስልጣን በመጨበጥ ይህንን መሪ አልባ መህበረሰብ ለመምራት ነው፤ ወደ ተስፋይቱ አለም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በአለም ዙሪያ "አብዮት" ያለ "መሪ" እና "ጥርት ብሎ ባልተደነገገ አላማ" ተደርጎ አያውቅም፡፡ በአመራሩ፣ በአላማውና በአስተዳደራዊ መዋቅሩ ያልተቀናጀ ንቅናቄ "ግርግር" እንጂ "አብዮት" አይባልም። የገዳ ስርዓት በኦሮሞ ህዝብ ውስጥ በተግባር የለም፡፡ ያለው በሊህቃኑ ምናባዊ rhetoric ውስጥ ነው፡፡

እንዲህ ያለም ንቅናቄ ውጤት አይኖረውም፡፡ ይህ "ፕሮፌሰር" ምንድን ሚቃዣው፤ የኦሮሞን ህዝብንስ በተግባር ምን ያህል ያውቀዋል? እኔ መቼም አያቴ እንኳን ይህንን ደንባራ ዘመን ሳያዩ ሞቱ ነው ያልኩት። እንደ እውነቱ የኦሮሞ ወጣት እንዲሁም የኦሮሞ ማህበረሰብ በጠቅላላው በገዛ ሀገሩ ባእድ ከተደረገ እና በሀገሩ ባይተዋር መሆን ከጀመረ አሁን ሐያ አምስ ዓመትተ ሆኖታል፡፡ እኔ ይህንን ከስተዋልኩ ቆይቻለሁ። ሐረማያ በሰራሁበት ዘመን የኦሮሚያ ተማሪዎች ሁሉን እርግፍ አድርገው "የባዕድ ኑሮ" ሲገፉ አይቻለሁ፡፡ ከግሩፕ ስራ አስተባባሪነት እስከ ትልልቅ ዩንቨርሲቲ አቀፍ የክበብ እንቅስቃሴዎች በተሳታፊነት እንኳን

“የሉበትም”፡፡ “በአመራር መሳተፍ” እማ አይታሰብም፡፡ በዩንቨርሲቲ የተጓዳኝ የትምህርት እንቅስቃሴ ያልዳበረ የአመራር ችሎታ በኋላ ከወዴት ሊመጣ ይቻለዋል? ከየክልሉ ከሚመጡ ተማሪዎች ጋር ያላቸው “መህበራዊ ተራክቦ” እጅግ ዝቅተኛ ነው።

“ይሄ ነገር ውሎ አድሮ ሀገር ይጎዳል፡፡ የኦሮሞ ተማሪዎች በተጓዳኝ ክበባት ተሳታፊ ለመሆን የማይፈቅዱበት፣በባይተዋርነት ከመህበራዊ ተሳትፎ እራሳቸውን ያገለሉበት ምክንያት ተጠንቶ ከወዲሁ መፍትሄ ካልተበጀለት ተተኪ የአመራር ችግር ይከሰታል” በማለት ለባልደረቦቼ አማክሬ ያተረፍኩት የፌዝ መሳለቂያነትን ብቻ ነበር። አሁን ውጤቱ መታየት ጀመረ። እስቄል ግን አልገባውም…ገዳ ምናምን ይላል፡፡

የገዳ ስርዓት “የጦርነት ግዜ ስርዓት” ስለመሆኑ እና ከዚህም “ጠባዩ” የተነሳ ዛሬ “ዲሞክራሲ” ከምንለው ፅንሰ ሀሳብ ጋር ምንም ተፈጥሮአዊ ቁርኝት ወይ ተመጋጋቢ-ተግባቢነት የለውም። የዚህ የኦሮሞ ማህበረሰብ በሀገሩ ባይተዋር የሆነበት ምክንያት ጥልቅ የባህል እና የታሪክ መሰረት ያለው ሆኖ እናገኘዋለን። በሚሶዮንያን ሴራ በብሄረሰብ የፖለቲካ አደረጃጀት ስም የኦሮሞኛ ቋንቋ “በላትን ፊደላት” እንዲፃፍ ሲደረግ ሰፊው የኦሮሞ ህዝብ ለዘመናት በፍቅርም ይሁን በጠብ ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋራ “ካዳበረው የባህል መሰረት ተነጠለ”። በዚህም ሳይበቃ የሰሜን ኢትዮጵያን ህዝብ ከደቡብ በዘርና በፖለቲካ “ድልድይ” ሆኖ ለዘመናት ያገናኘው የሸዋ ህዝብና መኳንንቱ በታሪክ ፊት “በወራዳነት” እንዲቀርቡ ሲደረግ “አኩሪ ታሪኩን” አጣ። ብሽሽታቸው እስኪላጥ ፈረስ ጋልበው ዘመናዊ ኢትዮጵያን የመሰረቱት የሸዋ የኦሮሞ መኳንንት “አሸብረቂ ታሪክ” ተሰርዞ “በባንዳነት” ተዋርደው ቀረቡ። በህወሓት “ሴራ” የሸዋ ግዛት “ከስድስት ክልሎች” ባላይ “እንዲከፈል” ተደረገ። ከዚህም የተነሳ የደቡቡና/በተለይ የኦሮሞና/ የሰሜኑ የኢትዮጵያ “ታሪካዊ ቁርኝት” ተበጠሰ።

በድምሩ በተለይ የኦሮሞ ወጣት “በሀገሩ ባይተዋርነትን” አተረፈ፡፡ ሀገራዊ ራዕዩም ተኮላሸ፡፡ ከተማዩ ሚለው አዲስ አበባ “አለ አግባብ” በኦሮሚያ “ተስፋፋ” በማለት “ግንባሩን ለጥይት ሲሰጥ”፤ አባቶቹ የሞቱለት “የሀገሩ ዳር ድንበር” ሲቆረስ እና “ለሱዳን ሲሰጥ” ብምን አገባኝነት ቆሞ “ተመልካች” ሆነ። … ለመደምደም ያህል የኦሮሞ ሊህቃን እንደሌሎቹ የኢትዮጵያ ልሂቃን በነበረው እየሞላ፤ የነበረውን እያዳበሩ ከመሄድ ይልቅ አፍርሰው ጀማሪዎች ሆኑ። እስካሁን እንከዋን የክልሉ ህገ መንግስት “ሁለቴ” ለውጠዋል፡፡ ባነድራውንም ግዜው ሲደርስ “ሊለውጡት” ተዘጋጅተዋል፡፡ ቢመርም እውነቱ ይህ ነው፡፡"……

ይላሉ ምሁሩ ከወዳጄ ጋር ያደረጉት ስለ ሰሞኑ እየቀጠለ ያለው የኦሮሞ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውይይት።

“fantasy የኢትዮጵያ ልሂቃን መለዮ ነው”። ያሉት ምሁሩ፤ተገንጣዮቹ ኢትዮጵያዊያን አይደለንም ቢሉም፤ “ክሕደቱን አኑሮው” በጨዋ ሞራል መናገራቸው ነው እና በኢትዮጵያ ሊሂቃን መለዮ ነው ሲሉ “ኦሮሞ” ነን የሚሉም ለመጨመር ነው። እኔ ደግሞ የምጨምረው “ፋንታሲው/fantasy” በሊሂቃኖቹ ብቻ ሳይወሰን በሚዲያ ባለቤቶችም ጭምር ነው።

አንድ ምሳሌ ልስጣችሁና ልደምድም” ወዳጄ ዶክተር አሰፋ ነጋሽና ፕሮፌሰር ጌታቸው ሃይሌ “ኢትዮሚዲያ” በተባለው ሚዲያ “ጠንከር” ያሉ “ለውይይት የሚጋብዙ” ምሁራዊ ትንታኔአቸው ለሕዝብቻን እንዳይተላለፍ የታገዱ ጸሐፊዎች ናቸው። የዚህ ሚዲያ አዘጋጅና ተባባሪዎቹ፤ እንዲሁም የመሳሰሉ ሚዲያዎች ‘ሥልጣን’ ላይ ቢወጡ ምን ያህል “ጨቋኝ” ይሆኑ እንደነበር ከወዲሁ ማየት ትችላላችሁ። ካሁኑኑ የመጻፍ መብት ሲያግዱ፤ መጪዋ የአገራችን ዕድል፤ ምን እንደምትመስል ግንዛቤ ካጠራቸው ከነዚህ “የሚዲያ ታይራንት” ግለሰቦች ይሰውራት የምለውም ለዚህ ነው።

ታሪኩ እንደዚህ ነው፡-

ዶክተር አሰፋ ነጋሽ ብቃት ያለው የፖለቲካ ተንታኝና የሕክምና ምሁር ነው። ደ/ር አሰፋ ነጋሽ፤ የኔው ብጤ ነው። “የፖለቲካ ኮረክትነስ/ድብብቆሽ/አድርባይነት/አይቶ እንዳላዩ...” ሆኖ ማለፍ የማይወድ ሰው ነው። ለሚዲያዎችም ሆነ ለተገንጣዮች “በእሱና በእነሱ መካከል” በሕዝብ ፊት ዲቤት/ውይይት/ እንዲደረግ ብዙ ጊዜ በይፋ “ጥሪ” አድርጎላቸው፤ ሊገጥሙት አልፈለጉም። “አጀንዳቸው” ዋጋ ቢስ መሆኑን የማጋለጥ በቂ እውቀትና ብርቱ ትንተና ማድረግ እንደሚችል ስለሚያውቁ ፤ እንዲሁም ወያኔዎች/ኦነጎች/ኦብነግ፤ በፓርቲ ስም፤ በሕዝብ ስም....ወዘተ....ብዙ ወንጀል እንደሰሩና incredibly corrupt and visionless/እጅግ የነቀዙ፤ራዕዬ-ቢስ/ መሆናቸው ማሕደራቸው በሚገባ ስለሚያውቅ፤ እስካሁን ድረስ ደፍረው “ግብዣው” ለመቀበል አልደፈሩም። ታዲያ የሕክምና ሊቅ እና የፖለቲካ ተንታኝ ዶ/ር አሰፋ ነጋሽ “Why Have the Amaras Once Again Become Victims of Ethnic Cleansing by TPLF? By Assefa Negash, M.D. 18th of April 2012 የሚል በ5 ክፍል የቀረበ ጽሑፍ፤ ለሕዝባችን እንዲዳረስ ‘ለኢትዮ-ሚዲያ’ አዘጋጅ ልኮለት፤ሕዝብ የራሱን ግንዛቤ እንዳይወስድ ሲያግድ ለተገንጣይ ቡድኖችና፤ አማራ ይቅርታ ይጠይቅ እያሉ ጥላቻን የሚዘሩ “የነገድ አቀንቃኝ ፖለቲከኞች” ግን ፕሮፓጋንዳቸውንና ፎቶግራፋቸውንም ጭምር ሳይሰለች ለብዙ አመታት እስከዚቹው ደቂቃ ድረስ እየዘረጋላቸው ይገኛል። ኢትዮ ሚዲያ ብትጎበኙ የምታዩት የተገንጣዮችና ጠባብ ጎሰኞች ፎቶግራፍና የፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳ ጹሁፎችን ነው።

ደ/ር አሰፋ ነጋሽ ዘገባ እንዲህ ይጀምራል፤

“***“A pregnant woman who only gave birth to a child during the night was thrown out on the street the following morning along with her mattress and child who is just a few hours old (neonate). Pregnant***

***Amara women have been forced to flee their homes. Many children as young as 8 months of age have been locked up in prison along with their lactating mothers and they have nothing to eat or drink thereby suffering from hunger. ……"***

እያለ በ5 ክፍል ተዘጋጅቶ ከአገር ባማርኛ የተዘገበውን ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞ የዘገበው የአማራ ሕብረተሰብ ሰቆቃ እንዲለጥፈው የላከለት ጽሁፍ "አቶ አብርሃ በላይ" አላትምምብ ሲሉ አምቢ አለ። በዚህ አብርሃ እና ደ/ር አሰፋ ነጓሽ የደብዳቤ ምልልሳቸው እንዲህ ይነበባል። (ካሁን በፊት ለጥፌላችሁ እንደነበር ትዝ ይለኛል)፤

"Greetings from Holland. I am sending you an article which has been broken down into five parts. Please post it on your website. You may not like all the content of the article, but I trust that you would accept the right of contributors like me to hold different opinions. I fully take responsibility for any opinion I express in this article and as I have stated clearly at the end of my article, I am ready to accommodate any perspective that challenges my views. So let me know whether you post it or not.

With best regards,
Assefa Negash

የአቶ አብርሃ በላይ አምቢታ የእምቢታ መለስ እንዲህ ይነበባል፡-

**From:** Editor <editor@ethiomedia.com>
**Date:** 19 april 2012 08:44:30 CEST

Dear Dr Assefa Negash,

My apologies for my delayed response!

To begin with, this short reponse shouldn't in anyway be mistaken for an invitation to engage you in a dialogue over the differences you and I've over the situation in Ethiopia.

For instance, a sentence from your piece reads: "In present-day Ethiopia the only people who are not adversely affected by this rule are the Tigreans who as members of

the ruling Tigrean regime have every right to settle in every part of Ethiopia and prosper even at the expense of others."

We are worlds apart, brother.

For you, TPLF means the Tigrai people and vice versa.

Though I wrote for years to persuade fellow compatriots like you that the ruling class is strictly an anti-Ethiopia mercenary class, such literature has fallen on deaf ears because brothers like you have made up their minds that Tigrians are in power and the people of Tigrai are beneficiaries of the 'Tigrian regime.'

That is the whole point in a nutshell.

But again, you are entitled to your opinion as I'm to mine. I'm not going to post your article because I believe - with all due respect - your article is not only wrong but also misleading, and detrimental to the unity of the Ethiopian people.

I'm writing this as an Ethiopian journalist, and not because I was born into a Tigrian family. I would have rejected (and I've done it several times in the past) if I were asked to post an article that in anyway tarnishes the image of the Amhara, Oromo etc people. For instance, a few days ago, an article written by Prof Getachew Haile about the Oromo people was removed from our website shortly after it was posted because there were lines that cast our Oromo people as 'invaders' and much worse.

I hope such denial of service wouldn't in any way strain our friendship.

Warmest regards,

Abraha Belai, Editor

የአማራ ሕብረተሰብ ሰቆቃ ለመላ ዓለምና ለሕዝባችን ለመንገር በመረጃ የተዘጋጀ እንዳይሰራጭ ያገደበት ምክንያት መልስ ሲሰጥ የሰጠው ምክንያት በራሱ ቃል “brothers like you have made up their minds that Tigrians are in power and the people of Tigrai are beneficiaries of the 'Tigrian regime.' ይላል። ስለሆነም ትግሬዎች ሥልጣን ላይ ሳይወጡ ሥልጣኑን ተቆጣጥረውታል ማለትህና፤ትግሬዎች በዚህ ሥርዓት ተጠቃሚ ሳይሆን ተጠቃሚ ነው…” የሚል እምነት ስለያዝክ “አልለጥፍልህም!” ሲል ማጠቃለያ ምክንያቱ ይህ ብቻ መሆኑን ገልጾለታል። That is the whole point in a nutshell. ሲል በግልጽ አምቢታው ግልጽ አድርጓል። ትግሬዎች ሥልጣኑን ተቆጣጥረውታል ለማለት “አማራን ሰቆቃ” ምክንያት አድርገህ በሽፋን የመጣኸው ‘በወያኔ ዘመን ትግሬዎች ተጠቃሚዎች ናቸው፤ ትግሬዎች ሥልጣን ላይ ናቸው” ለማት ስለፈለግክ ነው” ሲል ጽሑፉን ላለማተም አብርሃ የሰጠው ምክንያት ያ ነበር።

ተቃዋሚዎች ነን እያሉ እነዚህ ውጭ አገር የሚኖሩ “ሚዲያዎች” ኢትዮጵያዊያን አርበኞች የሚጽፉትን አስተያየት አናስተላልፍም እያሉ፤ ተገንጣዮች ግን “በቀጣይ” የሽፋን መብት፤ ከነሰንደቃላማቸው በቪዲዮ እየተቀረጸ ሽፋን ሲያደርግላቸው አይተናል። እነዚህ በተቃዋሚነት የቆሙ “ነፃ ሚዲያ ነን የሚሉ ነፃነት የሚያፍኑ ሚዲያዎች” ግማሾቹ ከጠባብ ጎሰኛነት ስሜት አጥር መውጣት ያቃታቸው ሲሆኑ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ “በፖለቲካ ድርጅት ፍቅር” የተተበተቡ “ድርጅት ሙርኮኞች” ናቸው። ወደ “ታች የሚንሸራተቱ” ትናንሽ ሕሊና ያለቸው መሆኑን ብቻ ሳይሆን፤ የፖለቲካው ግንዛቤአቸውም እጅግ የጫጫ መሆኑን ነው የሚያሳየን።

የአብርሃ ክርክር ከስሜት የማኢወጣ ፤ጭብጥ የሌለው መከላከያ ነው እየሞገተ ያለው። ሌላው ዝርዝር የጥናት ድጋፍ ያላቸው መረጃዎችን እንተወውና “ጥልቅ ምርምር” የማይጠይቀውን የወልቃይት ሕዝብ መሬት በትግሬዎች የመነጠቁ እውነታ/ ’ሄጂመኒ/ አነክሴሽን’፤ ትግሬው ሰፍሮበት በዓይኑ እያዬ (መነጋጋር ጀምርን በነበረበት ጊዜ ይህን መረጃ ለአብርሃ በላይ በስልክ ነግሬው ነበር)፤ ‘ትግሬ አልተጠቀመም፤ስልጣን ላይ አይደለም’ ብሎ መካድ የግንዛቤ እጥረት ብቻ ሳይሆን፤ አብርሃና መሰል የትግሬ ሊሂቃን ለራሳቸው ግልጽ በሆነ፤ እነሱ በሚያውቁት ምክንያት ለኛ ግልጽ ባልሆነ መከራከያ “ትግሬ አልተጠቀመም፤ ሥልጣን አልያዘም” እያሉ ይክዳሉ። ይህ ደግሞ “እስር ውስጥ ያለው “አብርሃ ሐጎስም” ጭምር ሲያካሂደው የነበረ መስመር ነው።

የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ፖለቲካ ሳይንስ መምህር የነበረው ታሳሪው አብርሃ ሐጎስም “ወያኔ ዘረኛ አይደለም፤ ወያኔ በግለሰብ እንጂ በማሕበረሰብ ላይ፤ማለትም በአማራ ላይ ዘረኛነት አላካሄደም።” “የግለሰብ አፓርታይድ ግን አካሂዶ ሊሆን ይችላል።” “ወያኔ አፓርታይድ

አይደለም"፤ "ትግሬ ስልጣን ለይ የለም፤ትግሬ አልተጠቀመም"፡ "ጃዋር መሐመድ ፖለቲካ ይመቸኛል"....ወዘተ....ወዘተ....ሲል ይከራከር እንደነበር የሚታወስ ነው። የወያኔ ፖሊሲ "በአማራ ሕብረተሰብ" ላይ የጻፈው "ቁልጭ ብሎ" እየተነበበ ያለው የወያኔ የትግል መነሾ፤ "አብርሃ ሐጎስ" ሙልጭ አድርጎ ሊያሞኘን የፈልጋል።
ሚዲያዎችም በዚህ ዓይነት "ስካርና ክሕደት" አልፎም "አጉል የፖለቲካ ጊዜያዊ ድጋፍ ለማግኘት በእወደድ ባይነት" አብረው አየነጐዱ ናቸው። እንዲህ ያለ ጉድ ተሸክመውም ቢሆን ዛሬም ለጠባቦችና ለገንጣዮች ሚዲያዎች ክፍት አድርገው እያገለገሉ ናቸው።

ባይተዋር ኦሮሞ ተማሪዎችም፤ "ማይምነትን" ያለበሷቸው የኦሮሞ "ፋሺስታዊ ምሁራን" ከመቃወም ይልቅ አገራቸው ኢትዮጵያን በመካድ፤ በጠባብ ክልል ተከልለው "ወደ ፋሺዝም" እያመሩ "ግራ በመጋባት ላይ ናቸው" ናቸው። ወዴት እያመሩ እንደሆነም በቅጡ ይወቁት እንጂ ምን እንደሚገጠማቸው አላወቁትም። መፈክራቸውና ንግግራቸው የሚደመጠው ኦሮምኛ ስለሆነ፤ የተቀረው ኢትዮጵያ ህዘብ ምን እያሉ አንደሆነ ማወቅ አልቻለም። እየተገለሉ ባይተዋርነት እያጠቃቸው ነው የምልብትም ነጥብ ለዚህ ነው። ሕዝቡ ምናቸው ተረድቶ ይደግፋቸው? አገራዊ የመገናኛ ቋንቋችን አማርኛ እንዳይናገሩና እንዳኢማሩ በላቲን ፋሺስታዊ ሊሂቃን ፖሊሲ ታግደው ወደ ድቅድቁ የድንቁርና "ጭለማ" ተገፍትረው ሙሉ በሙሉ ባሳዛኝ ሁኔታ ተፈርዶባቸው እስከወዲያኛው በማይምነት ሰንሰለት ታስረው ገበተዋል።ሕዝባችን በምናቸው ይረዳቸው። ኦሮምኛ አንኳን መላይቱ አገሪቱን በ24 አመት ለማስተዋወቅ ቀርቶ ካሁን ወዲያ በ700 አመት ውስጥም ሕዝቡ አንደ አማርኛ ተሎ አገራዊ መገናኛ አያደርገውም። ምክንያቱም ቋንቋ ለመስፋፋት "የራሱ ልዩ ሂደቶችና ሕጎችን" ተከትሎ በገበያና በመሳሰሉት ያደገ ነው። ኦሮሞዎች ደግሞ የተከተሉት "ላቲን" ነው። ከተቀረው ህዝብ ጋርም አንዳይገበያዩ እና እየተዘዋወሩ አንዳይሰሩ "በክልል ቋንቋቸው ታስረው፤ እራሰቸው ባኢተዋር ዓለም ገብተው፤ ወኪሎቻቸው ሳኢቀሩ በቲቪ ባስርጓሚ ነው መልክቶቻቸው የሚያስተላልፉት። አሰዛኙ ክስተት ይኼ ነው። የሊህቃኑ ደካማነት ቢያስቅም፤በወጣቱ ላይ የቋንቋ ጥላቻ እንዲአድርበትና፤አገራዊ የመረዳጃ "ቋንቋ" አማርኛን "የመማር እገዳ" የጫኑበት ወንጀል ግን እጅግ አሳዛኝ ነው። ውሎ አድሮ ይህ በራስ ባኢተዋርነት ችግር እንደሚመጣ እናውቀው ነበርና ፤ ጊዜው ደርሶ ሕዝቡ ተማሪዎቹ ሲሰለፉ፤መልእክት ሲያስተላልፉም ሆነ መፈክር ሲያስተጋቡ ምን እያሉ አንደሆነ ሊገባው አልቻለም።ስለሆነም፤ ሕዝቡም አንደ ዩክረይን እና አረብ ተናጋሪዎች የሚሉትን ሳይገባው በቴ/ቪዥን እያያቸው፤ ምን አንደሚሉ ሳይገባው "አግራሞቱ" በታዛቢነት እየቀጠለ ነው።

በሌላ በኩል አስተርጓሚ ሆነው ሚቀርቡት (ሕዝቡ የኦሮሞ እንቅስቃሴ መረጃ የሚነግሩት) ደግሞ ተቃዋሚ የሚባሉት እነ ጠባብ ብሔረተኛ አቀንቃኙ መራራ ጉዲና እና ተምበርካኪው ጻረ አማራው "የሰማያዊው ፓርቲ መሪ" ተብየው ይልቃል ጌትነትና መሰል ተቃዋሚዎች በኩል ነው። የእነዚህ ደላላዎች ትክለሰውነት እየቀባቡ ሳይሰለቻቻው ሽፋን የሚሰጡዋቸው ደግሞ በበኩላቸው "ሚዲያዎች" ናቸው። ሆን ብለው የነዚህ ተምበርካኪ ሰዎች ተክለሰውነት እያሞገሱ ለ24 አመት አብረው ዘልቀዋል። አስገራሚወ ግን፤ እያደር ቃርያ የመሆናቸው ትዕይንት ሕዝቡ ቀስ በቀስ የገባው ይመስላል (ዲአስፖራ ጀሌዎችን ትተተን

ማለት ነው)። ሕዝቡ መቆራጥ መሪ አጥቶ፤ ወያኔ ለ24 አመት ለምን በብልግና እየተጨማለቀ እንደቆየ የሚዲያዎችና የተቃዋሚዎች "ደላላነት፤ተባባሪነት፤ አታላይነትና እከከን ልከክልህ" ባሕሪ መሆኑን አውቆታል ። ሕዝባችን እነዚህ "ሚዲዮክር" (ዕርባና ቢስ) ተቃዋሚዎችና ሚዲያዎች፤በአፈጮሌነት እየተነዱ እስከዚህ ድረስ ደርሰዋል። ትናንት እንዳልረቡዋችሁ ሁሉ ዛሬም ሆነ ነገ አንደማይረቡዋችሁ አወቁት። የኦሮሞ ተማሪዎችም ይህ ሁሉ የኦሮሞ ወጣት በወያኔዎች ጥይት ሲረሸን፤ አውጭ አገር ተቀምጠው ምቾት የከበበው ኑሮ የሚመሩ እነ "ኢብሳና እነ ጃዋር፤ እነ እዝቄልና እነ መገርሳ...... የታወቁ አነግ ጀሌ ሙዚቀኞችና ሙዚቀኞች" "ግፉ በለው" "አሮሚያ ኬኛ" ከማለት አልፈው ወደ "አሮሚያ ኬኛ" ጠመንጃ ማንገትም ሆነ ወደ ሰልፉ ወላፈን "እራሳቸውና ልጆቻቸው ልከው ለመቀላቀል" አንደማይደፍሩ " አገር ውስጥ ያሉት ተማሪዎቹ፤ከልባቸው ይህንን የሊሂቃና አታላይነት "ከመኔሶታ አዳራሽ መፈክር ማስተጋባትና በቲቪ/ራዲዮ መለፍለፍ አልፈው፤ እራሳቸውንና ወጣት ልጆቻቸውን መስዋእት ለመሆን ወደ ኢትዮጵያ/አሮሚያ ወደ እሚሉት ክልል ትግሉን ለመምራት ዝግጁ አንዳልሆኑ" ተማሪዎቹ ቀስ በቀስ አንደሚረዱት ያውቃሉ። ከዛው ማሃምነትና ባይተዋርነት ለመላቀቅ የጊዜ ጉዳይ እንጂ "የምንሰማው ጉድ" ሩቅ አይሆንም።

እነዚህ ግፋ በለው ተገንጣይ አቀንቃኞች፤ እንኳን ወደ ኢትዮጵያ መዳዝ ቀርቶ ፤ጠመንጃ እንካችሁ ወደ እሚላቸው ወደ ኤርትራ ሄደው የሚዋሹላትን "ኦሮሚያ" የምትባል "ነፃ" ለማውጣት ለመሄድ አልከጀሉም። የፒዛ "ሱስ" ሃይለኛ ነውና፤ የሚያድርጉት አታላይ ባህሪያቸውን ምን አንደሚመስል እራሳቸው ያወቁታል።ምስኪን የኦሮሞ ገበሬ ልጅ ግን ባይተዋር ሆኖ፤ የፖለቲካቸው ሰለባቸው የመሆኑን ክስተት እጅግ ያሳዝናል።

<u>ለማጠቃለል</u>

እየታየ ያለው የኦሮሞ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ክልላዊ የነገድ ጥቅም አስከባሪ ከመሆን አልፎ፤ የመገንጠል ጥያቄን እና ባይተዋርነትን የሚያጎለብት "ኢትዮጵያዊ ግንዛቤ የሌለው" ሥር ነቀል የስርዓት ለውጥ የማያመጣ፤የአገሪቱን አስኳል አናግቶ "መሪ የሌለው ወደ አናርኮ ፋሺዝም" የሚመራ፤ "ራዕዬ ቢስ" የተገንጣዬች አብዮት መሆኑን ዛሬም በድጋሚ እንድታወቁት ግንዛቤአችሁ አስተካክሉ። ፓኪስታን/ኤርትራ/ሶማሊ/....የመሳሰሉ በጭቆና፤በወረበሎች፤ በነገድና በሃይማኖት ግጭት እየታመሱ በመዋለል፤ ለቀውስ የዳረጋቸው ምክንያት የዛው አካባቢ ምሁራኖች "የነቀዘ ሕሊና" ስራ ላይ ሲውል የታዬ አሳዛኝ ውጤት ነው። በተለይ የኦሮሞዎችና አጋዴኖች የግንጠላ አቀንቃኝ ምሁራኖች "በወንጀል የተጨማለቁና የተሳተፉ ነብሰገዳዮችና ፋሺስት ርዕዮት ያነገቡ ድርጅቶች ስለሆኑ" በዚህ የነቀዘ መስመራቸው ከቀጠሉ፤ አመራር ብቃታቸው እጅግ ቡዱናዊና ጎሳዊ ስለሆነ በአካባቢያቸው ያለው እና ከስራቸው ውስጥ የሚገኝ ኗሪ "ወደ ባሰ የነገድና የሃይማኖት መተረማማስ" ግጭት እንደሚያስገቡት ጥርጥር የለኝም። ወደዚያውም እያመሩ አንደሆነ ተከታዮቻቸው በጥንቃቄ ሊያዩት ይገባል። ቴምፐራሪ ፊክስ "ጊዜያዊ ምርቃና እንጂ" ዘላቂ "ኢፎርያ" የተላበሰ "እፎይታን" አያመጣም።ይቀጥላል.......አመሰግናለሁ- ጌታቸው ረዳ (Editor Ethiopian Semay) getachre@aol.com